# መጽሐፈ፡ ጨዋታ።
# ሥጋዊ፡ ወመንፈሳዊ።

በ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ከዘነበ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተጻፈ ።

፪ኛ ፡ በመርሐ ፡ ጥበብ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።
፲፱፻፵፬ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ አበባ ።

ዋጋው ፩ ብር ።

## መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡ ሥጋዊ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

እግዚአብሔር ፡ እስቲሻር ፡ ሚካኤል ፡ እስቲሦት ፡ ምንነው ፡ በኖርሁኝ ። ገብርኤል ፡ ሲያንቀላፋ ፡ ሩፋኤል ሲደክም ፡ ሐሰተኛው ፡ ዲያብሎስ ፡ ንስሐ ፡ ይገባል ።

ክረምት ፡ ሲመጣ ፡ ሰማይ ፡ እንዲከብድ ፡ የበሉትም ሰው ፡ ሲመጣ ፡ እንደዚያ ፡ ይከብዳል ። ዘወትር ፡ ከሚያጋድል ፡ አሀያ ፡ ተሸክሞ ፡ መሄድ ፡ ይሻላል ። ከማያስተካክል ፡ መሳከተኛ ፡ የማለዳ ፡ ወፍ ፡ ትሻላለች ፡ ምንነው ፡ ቢሉ ፡ ንጋቱን ፡ ትነግራለችና ።

ደንጋይና ፡ ጭቃ ፡ ቢቀባበሉ ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ረጅም ቅጥር ፡ ይሆናሉ ፡ እናንተም ፡ መሬታውያን ፡ ሰዎች ፡ እንደዚህ ፡ ብትረዳዱ ፡ ጥበበኞችሁና ፡ ኃይላችሁ ፡ ከሰማይ ፡ በደረሰ ።

ከሰና ፡ ክረምት ፡ ፊት ፡ ይመራል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ደስ ያሰኛል ። ድሬ ፡ ምንደር ፡ ነው ፡ ገንዘብን ፡ ለመቆፈሪያት ፡ የተሠራ ፡ ሰንሰለት ፡ ነው ። እሬት ፡ መብላት ፡ ቢለመድ ፡ ባልተለቀቀም ፡ ነበር ፡ ዝሙትም ፡ ሳለመደው ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

ጣዝማ ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ ናት ፡ መሬት ፡ ቀዳ ፡ ገብታ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሆን ፡ ማር ፡ ትሠራለች ። ምነው ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ወይ ፡ ከፈጣሪ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ብልሀትን ፡ አትፈልጉምን ።

የምሥራች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ ባሕር ፡ ይሰጥማል ። እርጎን ፡ ከፍቶ ፡ ቢተውት ፡ ዝንብና ፡ ድመት ፡ ይጫወትበታል ፡ አገርንም ፡ አቅንቶ ፡ ሰው ፡ ካላስቀመጡበት ፡ ተመልሶ ፡ ዱር ፡ ይሆናል ።

ባቤቱ ፡ የሚከፋ ፡ ሰው ፡ ጅል ፡ ነው ፡ የሰው ፡ እቤቱ፡ እንድ ፡ አዳም ፡ አይደለምን ። ሴትን ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ይደርስባታል ፡ መንታ ፡ ትወልዳለች ፡ እህልም ፡ እንዲት ፡ ፍሬ ፡ ተዘርቶ ፡ ብዙ ፡ ታፈራለች ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ እንጃ ፡ ማን ፡ ያውቀዋል ፡ ያ ፡ የጠቢቦች ፡ ጠቢብ ፡ ያውቀው ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ እንጃ ።

ፈረስ ፡ በብረት ፡ ልጓም ፡ ይገታል ፡ የሕዝብም ፡ ልጓሙ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ መቃብር ፡ መልከም ፡ ጉታ ፡ ነው ፡ ብስሉንና ፡ ጥሬውን ፡ ይከታልና ። ወዳጅ ፡ ቢወዱት፡ ይወዳል ፡ መሬትም ፡ ቢበሉት ፡ ይበላል ።

በርበሬ ፡ ላዩን ፡ ቀይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ በብልሐት ፡ ገብቶ ፡ ሊለበልብ ። ክፉ ፡ ሰውም ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ኋላ ፡ ነገሩን ፡ ያመጣል ።

ቸር ፡ ሰው ፡ ለመጻጺ ፡ ጠጅ ፡ ነው ፡ ፍቅሩ ፡ ያሰክራልና ። ዝናም ፡ ከዘነመ ፡ በኋላ ፡ ቡቃያ ፡ ያበቅላል ፡ ንጉሥም ፡ ከመደደ ፡ በኋላ ፡ ይሾማል ።

ሸክላ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ውሀ ፡ አርሶ ፡ አሠርቶት ፡ መከታ ፡ እየሆነ ፡ እሳትን ፡ ያስወጋዋል ። ክፉም ፡ ሰው ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ወንፊት ፡ ዱቄትን ፡ እንዲነፋ ፡ ዘርዛራም ፡ ሸማ ፡ ጠጅን ፡ እንዲያወርድ ፡ ባለቤቱም ፡ ያልቻለውን ፡ ምሥጢር ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ አይችለውም ።

ቅቤ ፡ ከዶብና ፡ ከጓት ፡ እንዲለይ ፡ ፀባዩም ፡ እንዲሆን ፡ ጻድቅም ፡ ሰው ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

ደመና ፡ ሰማዩን ፡ እንዲሸፍነው ፡ ንጉሥም ፡ በሠራዊቱ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ሳማና ፡ አብላሊት ፡ ለምለም ።

መስለው ፡ እንዲሰበልዙ ፡ መናፍቃንም ፡ ሲቀርቧቸው ፡ እንደዚያ ፡ ናቸው ።

በቀስታና ፡ በዝግታ ፡ የተበጀ ፡ መዘጦር ፡ ኋላ ፡ ጉልበት ፡ ይሆናል ። ወረቀት ፡ መልክም ፡ እርሻ ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይዘራልና ። ጉታም ፡ አይሻ ፡ እርሱ ፡ ከቶት ፡ ይኖራልና ።

ማር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያገለግላል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መበጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መብራት ፡ ሆኖ ። ምነው ፡ ቢሉ ፡ የብልሕ ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ አሰርጓም ፡ የለው ።

ሕዝብና ፡ ሕዝብ ፡ ደጋና ፡ ቆላ ፡ ናቸው ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ገበያ ፡ ነው ፡ ሁሉን ፡ ያገናኛልና ። ሸክላ ፡ ከተሰበረ ፡ በኋላ ፡ ገል ፡ ነው ። መኳንንትም ፡ ከተሻሩ ፡ በኋላ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

ክፉ ፡ ሰው ፡ ሽንቱን ፡ በሸነ ፡ ጊዜ ፡ ኋላ ፡ ጉንፋን ፡ ያዞርናል ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ግብሩ ፡ ተጉደፍ ፡ የተወሐደ ፡ ነውና ፡ ማርና ፡ አሬትን ፡ በመገዙ ፡ ማን ፡ ይደፋል ፡ አሬት ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ክፉ ፡ መራራ ፡ ነውና ።

ከብዙ ፡ ቀን ፡ ደስታ ፡ የንድ ፡ ቀን ፡ መከራ ፡ ይበልጣል ። ንጉሥ ፡ ምሰሶ ፡ ነው ፡ ሠራዊት ፡ ግድግዳ ፡ ናቸው ። መኳንንት ፡ ግን ፡ ማገር ፡ ናቸው ፡ ለንቋጣ ፡ ልጡ ፡ እንዲጣልባ ፡ እንጨቱም ፡ ቀሊል ፡ እንደሆነ ፡ ጠስላታም ፡ ወዳጅ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

ጨዋ ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይዞራል ፡ ምናልባት ፡ ሰልችተው ፡ ይተውኛል ፡ ብሎ ፡ ነውን ፡ ከሬት ፡ ጋራ ፡ ይጋባ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚለቀው ፡ የለም ።

አንድ ፡ ዓይንና ፡ አንድ ፡ ዓይን ፡ ያላቸው ፡ ተጋብተው ፡ ሁለት ፡ ዓይን ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ወለዱ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ ከበቱ ፡ አንዱ ፡ ከናቱ ፡ ነዋ ። የዚህ ፡

ዓለም ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ ጥጋብና ፡ ኵራት ፡ ነው ። ኵራት ፡ ምንድር ፡ ነው ፣ እን ደርሱ ፡ ሆኖ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሰው ፡ መናቅ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ፍሪዳን ፡ አብልቶ ፡ አብልቶ ፡ ያሰባዋል ፡ በመ ጨረሻውም ፡ ይበላዋል ። ምነው ፡ ቢሉ ፡ አብልቶ ፡ መብ ላት ፡ እንጂ ፡ ገበያ ፡ ነው ። ወርቅ ፡ ቢያብረቀርቅ ፡ ብር ፡ ያብለጨልጫል ፡ ምነው ፡ እናንት ፡ መናፍቃን ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ብልሐት ፡ አታዋጡምን ።

የዝንብ ፡ ብልሐቷ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ሌላው ፡ የሠራ ውን ፡ መብላት ፡ ነው ። ሰነፎች ፡ ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ መብላት ፡ ይወዳሉ ።

ደሀ ፡ ከመሆን ፡ ሀብታም ፡ መሆን ፡ ይሻላል ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ አይናገርምና ። በምድር ፡ ከመኖር ፡ በሰማይ ፡ መኖር ፡ ይሻላል ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ መከ ራው ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

ከባለጌ ፡ ፍቅር ፡ የንጉሥ ፡ ቁጣ ፡ ይሻላል ፡ የረሀብ ፡ ጌት ነቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ አህል ፡ በታጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ የሌለውን ፡ አምጡ ፡ ይላልና ። የማጣትስ ፡ ጌትነቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የፈለጉት ፡ ነገር ፡ በታጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የጥጋብስ ፡ ጌትነቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የመብላትስ ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ጥጋብ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

ሥራ ፡ ሳትሠራ ፡ በስንፍና ፡ ከሌጋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ከምት ውል ፡ ሴት ፡ ገጣባ ፡ አህያ ፡ ይሻላል ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ጭኖ ፡ ያበላልና ።

ጉጠት ፡ የበረደውንና ፡ የጋለውን ፡ ብረት ፡ እንዲይዝ ፡ አብድ ፡ ሰውም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። መቃጥንና ፡ ብልሀ ።

## መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡ መንፈሳዊ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

ቀቤ ፡ ለመጽሐፍ ፡ ዘመዱ ፡ አይደለም ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ቀቤ ፡ ነው ፡ አታክልት ፡ ሆኖ ፡ ካላፈራ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካልፈራ ፡ መቆረጥ ፡ አይቀርለትም ። ኮትኳችና ፡ አራሚ ፡ የሌለው ፡ አትክልት ፡ አይረባም ፡ ንጉሥና ፡ መምሕር ፡ የሌላትም ፡ አገር ፡ እንደዚህ ፡ ናት ፡ ኃጢአት ፡ ስትሠራ ፡ ደስ ፡ ይላታል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ፍሬ ፡ ስታፈራ ፡ ፍሬዋ ፡ እሬት ፡ ይሆናል ።

ከረጢት ፡ መሰፋቱ ፡ ለወርቅ ፡ መያዣ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልብም ፡ መፈጠሩ ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለማወቅ ፡ ነው ። የጻድቅ ፡ ልብሱ ፡ እሾህ ፡ ነው ፡ የዲያብሎስም ፡ ልብሱ ፡ ክፋት ፡ ነው ።

ሸንኮርትና ፡ ድንች ፡ ፍሬያቸው ፡ በሥራቸው ፡ እንደ ሆነ ፡ ጻድቃንም ፡ በሥራቸው ፡ ለማፍራት ፡ የአምላካቸውን ፡ ነገር ፡ በልባቸው ፡ ይተክላሉ ።

በገና ፡ ሆዱ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ለወፍራሙም ፡ ለቀጭኑም ፡ እንደ ፡ ጠባያቸው ፡ እንደሚፈሥህ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደጠባዩ እንደ ፡ ጠባዩ ፡ ይሰጠዋል ።

የተምር ፡ ፍሬ ፡ እንዲጣፍጥ ፡ የጻድቃንም ፡ ሥራ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ ቅል ፡ በዝናም ፡ ይበቅላል ፡ ሸክላም ፡ በውሀ ፡ ይሠራል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ለወሀ ፡ ማደሪያ ፡ ይሆናሉ ።

ሰውንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ በኋላ ፡ መልክም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንዲሆን ፡ ማደሪያው ፡ ያደርገዋል ። መሳል ፡ መልክም ፡ ነው ፡ ብረትን ፡ ይስለዋልና ፡ መጽሐፍም ፡ መልክም ፡ ነው ፡ ልብን ፡ ያበራዋልና ።

እግዚአብሔር፡አዮግ፡አረጀ፡ዘመኑንም፡የሚያውቀው፡ ታጣ ። መጽሐፍ፡ መንጸር፡ ነው፤ ለሚመለከተው፡ ሰው፡ ከሩቅ፡ ያሳያልና ። ሰነፍ፡ ሰው፡ በሰው፡ ይታመናል፤ ኋላም፡ ተመልሶ፡ ጠላት፡ ይሆነዋልና፡ ምንም፡ አያገኝ፡ እግዚአ ብሔርን፡ ግን፡ ተስፋ፡ የሚያደርግ፡ ሁሉን፡ ያገኛል ።

በጥቂት፡ ደመና፡ የደጋ፡ መሬት፡ በረዶ፡ እንደ ሚያፈላ፡ እግዚአብሔርንም፡ በማይፈራ፡ ሰው፡ መከራ፡ ድንገት፡ ይደርስበታል ።

ነብር፡ ፍየልን፡ ተኩላ፡ በግን፡ ጅብ፡ አህያን፡ ሞጭ ሞጭላ፡ (ምጥማጥ፡) ዶሮን፡ እንደሚፈልጉ፡ ዲያብሎ ስም፡ የአዳምን፡ ልጆች፡ እንደዚያ፡ ይፈልጋቸዋል ።

የወጥ፡ ማጣፈጫው፡ ምንደር፡ ነው፡ ጨውና፡ ቅቤ፤ የሰውም፡ ማጣፈጫ፡ ሃይማኖትና፡ ምግባር፡ ነው ። የእ ግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ ከማፍረስ፡ አሬት፡ መብላት፡ ይሻላል ። ምነው፡ ቢሉ፡ በውሀና፡ በማር፡ ይሟሻልና ። የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ ግን፡ ያፈረሰ፡ ዘለዓለም፡ እንደ፡ መረረው፡ ይኖራል ።

እግዚአብሔር፡ አብ፡ ባት፡ ነው፤ እግዚአብሔር፡ ወልድ፡ ብዕር፡ ነው፡ እግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ቀለም፡ ነው፡ ሰማይና፡ ምድር፡ ወረቀት፡ ናቸው ። ፊደ ሉም፡ ፍጥረት፡ ነው ። እግዚአብሔር፡ አብም፡ በቃሉ፡ ሰማይንና፡ ምድርን፡ ፈጠረ ። ያለባቸውንም፡ ፍጥረት፡ ሁሉ፡ ፈጠረ ። በመንፈሱም፡ አጸናቸው ።

የወጥ፡ ማጣፈጫው፡ ምንደር፡ ነው፡ ጨጨውና፡ ቅመም፡ ቅቤም፡ ነው ። የሰውም፡ ማጣፈጫው፡ ሃይማኖትና፡ ፍቅር፡ ነው ። ሃይማኖት፡ ያለው፡ ሰው፡ ሁሉን፡ ያገ ዛል፡ ኤልያስ፡ ሰማይን፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከ፮፡ ወር፡ ዘጋ፡ ዝናብም፡ አልዘነበም ። ቀለም፡ በቀንድ፡ (በብልቃጥ፡)

መድፍ፡ሽክሙ፡የከበደ፡ነው።ነገር፡ግን፡በመንኰራኵር፡ ይሄዳል። ሰልፍም፡ለጊዜው፡የሚያስፈራ፡ግሩም፡ጭንቅ፡ነው። ማሸነፍ፡ ግን፡ በሀብት፡ ነው፡ እንጂ፡ በጉልበት፡ አይደለም ።

በለዓም፡ እስራኤልን፡ ለመርገም፡ ለምን፡ ይሄዳል፡ ምርቃትን፡ ያዕቆብ፡ ሠርቆ፡ እንዳመጣት፡ አያውቅምን፡ አህያዪቱ፡ እንኳ፡ ከለከለችው፡ ለክ፡ በጊዜው፡ መሥረቅ፡ መልከፃ፡ ነው ። ኮከብ፡ ከያዕቆብ፡ ሲወጣ፡ አየሁ፡ ይላል፡ ያዕቆብን፡ ሰማይ፡ ማድረግ፡ ነውን ።

ባላቅስ፡ በጉን፡ ለምን፡ በየተራራው፡ ይፈጃል፡ ያዕቆብ፡ እንዲሆን፡ የበግ፡ ለምድ፡ ለበሰ ። ቀስ፡ ብሎ፡ ግብቶ፡ ከኤሳው፡ የነጠቃት፡ ምርቃት፡ ናት ።

እንዲያውስ፡ ፈጣሪውን፡ ሌሊት፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ታግሎ፡ የጣለ፡ አይደለምን፡ ፈጣሪውን፡ ያሸነፈውን፡ እኔ፡ እችላለሁ፡ ብሎ፡ ነውን፡ ደግሞስ፡ ያማቱን፡ በጎች፡ እንጨት፡ አዝንርጉሮ፡ እያሳየ፡ ገና፡ በማሕፀን፡ ሳሉ፡ ዝጉርጉር፡ እያደረገ፡ ለቅሞ፡ የወሰደበት፡ እርሱ፡ አይደለምን፡ ወንድሙንስ፡ ገና፡ በማሕፀን፡ ሳለ፡ ያሰነከከለ፡ እርሱ፡ አይደለምን፡ ባላቅ፡ ሆይ፡ ተው፡ ይህ፡ ሰው፡ ረቂቅ፡ ደጅን፡ ይኖረዋል፡ ልያስ፡ ከራሔል፡ ጋራ፡ ምን፡ ያጣላታል፡ ወይስ፡ እንደ፡ ሎጥ፡ ሚስት፡ ጨው፡ መሆን፡ ይፈልጋታልን፡ ስለ፡ ዝሙት፡ ይልቅ፡ በልጅዋ፡ እንከይ፡ መግዛት፡ ይሻላታል፡ ሎጥ፡ ልጆቹን፡ የደገማቸው፡ እንደ፡ እናታቸው፡ ጨው፡ ይሁኑ፡ ብሎ፡ ነውን ።

## መጽሐፈ፡ ጨዋታ፡ ወንጌላዊ ።

### ክፍል፡ ፪ ።

እግዚአብሔር፡ በደብረ፡ ሲና፡ በጁ፡ አሥር፡ ነገር፡ ዘራ፡ የሚያጭደውም፡ በታጣ፡ ጊዜ፡ አንድ፡ ልጁን፡ ቢ

ልከው ፡ እንግዳ ፡ ነውና ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ አደረ ፡ ይህንም ፡ አዝመራ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ብቻውን ፡ አጭዶ ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ አባቴ ፡ አባቴ ፡ አመስግነኝ ፡ አለ ፤ ምነው ፡ ከረኛ ፡ ቤት ፡ ተወለደ ፡ ብለን ፡ አምተነው ፡ ነበር ፤ አሁንስ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ እረኝነቱን ፡ ገለጠው ፤ ለከ ፡ የበጎች ፡ እረኛ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ከሰማይ ፡ ተሰዶ ፡ የመጣ ፡ በጎችን ፡ ሊጠብቅ ፡ ነውን ።

ከሰማይ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ በግ ፡ መጠብቅ ፡ ከልቀረለት ፡ ይህችን ፡ ታናሽ ፡ መንጋ ፡ መጠበቁ ፡ ለምንድር ፡ ነው ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ መንጋ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ጠብቆ ፡ ደመወዙን ፡ በምስጋና ፡ አውጥተን ፡ እንሰጠውምን ።

የተሰበረውን ፡ ጠግኖ ፡ የደከመውን ፡ አሳርፎ ፡ ተዞላ ፡ እንዳይነዋቃቸው ፡ ጠብቆ ፡ ከበጎቹስ ፡ መልከከሙን ፡ እየመረጠ ፡ አይወስድምን ። ቀበሮውንስ ፡ ያውቀው ፡ የለምን ፡ አንድ ፡ በግ ፡ በገኝ ፡ ጊዜ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ጉድጓድ ፡ እንደሚገባ ።

ያችም ፡ በግ ፡ ከረኛዋ ፡ ፈቃድ ፡ ወጥታ ፡ ከተገኝች ፡ መዳን ፡ የላትም ። ምነው ፡ እርሱ ፡ ባዘዛት ፡ ብትገባ ፡ ደጁ ፡ እርሱ ፡ አይደለምን ። አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ የኃጢአት ፡ ብርድ ፡ ቢያንቀጠቅጣቸው ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋን ፡ ለበሰ ።

በበረትም ፡ ወይፉ ፡ ወገኖቹ ፡ የላም ፡ እረኞች ፡ አዩት ፡ ለላም ፡ እረኞችም ፡ የምስራች ፡ ነገሩቸው ፤ ለከ ፡ እረኛ ፡ እረኛ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

በ፭ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ተዋረደ ፤ አንድ ፡ ልጁን ፡ ለሰው ፡ ባሪያ ፡ ሆነህ ፡ ሥጋ ፡

ከቶ ፡ ልጅነት ፡ አይቀርም ፡ ኢየሱስ ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ እማወት ፡ ብሎ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡ በርሱም ፡ ድንጋጤ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ። አባቱም ፡ ከላይ ፡ ሆኖ ፡ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ሲል ፡ ዋለ ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ርግብ ፡ ሆኖ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ዋለ ። ዮሐንስ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ እያለ ፡ ለምን ፡ ያሰየዋል ፡ ያለገዜው ፡ ይታረድ ፡ ብሎ ፡ ነውን ። ቢታረድስ ፡ የታደሉና ፡ የተመረጡ ፡ ጀግኖች ፡ ይበሉታል ፡ እንጂ ፡ ፈሪ ፡ አይበላውም ። እርሱም ፡ ምሥጢር ፡ አይችልም ፡ ብናበላውና ፡ ብናጠጣው ፡ ከባቱ ፡ ዘንድ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረን ።

ለቀበሮች ፡ ጉድጓድ ፡ አላቸው ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ማረፊያ ፡ ዛፍ ፡ አላቸው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ የለውም ፡ ይላል ። ለካ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ቢጠበው ፡ ነው ፡ ከሰው ፡ ውስጥ ፡ መጥቶ ፡ ያደረ ፡ እንደባሪያም ፡ የመሰለ ።

ኢየሱስ ፡ ሠርግ ፡ በቢታንያ ፡ በቃና ፡ ዘገሊላ ፡ ወሀውን ፡ ጠጅ ፡ አድርጎ ፡ አጠጣ ፡ በሰው ፡ ሠርግ ፡ እንደዚህ ፡ የሆን ፡ በራሱ ፡ ሠርግ ፡ እንዴት ፡ ይሆን ። የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ሠርግ ፡ አይቷ ፡ ከደግሙም ፡ በልቷ ፡ ጠጥቷ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ምነው ፡ በሞትሁ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኑ ፡ ያባቱ ፡ ቡሩካን ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁን ፡ ውረሱ ፡ ይላል ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ምን ፡ ኖሮታል ፡ ጥበቡ ፡ አይታወቅ ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

እናንት ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ፡ አለ ፡ መብራት ፡ አብርቶ ፡ በእንቅብ ፡ ውስጥ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፡ ይላል ። ዓለምን ፡ ያሀል ፡ እንቅብ ፡ ደፋቶብን ፡ የለምን ፡ እኛ ፡ በወ

አባቶቻችንን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እያሉ ፡ ያወጣው፡ ገንዘብ ፡ ይበቃዋል፡ ባለጠጋ፡ ወደ ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ከሚገባ ፡ ገመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ መሔድ ፡ ይሻላል፡ ይላል። ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ባለጠጋ፡ አለን፡ እርሱ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይኖር ፡ የለምን ፡ ይህንን ፡ እያመከኝ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ፡ አሸግሮ ፡ ማየቱ ፡ ምንድነው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እሥሩን ፡ ትናግር ፡ ተናግሮ፡ ከወንጌል ፡ አደረሰን አታስቡ፡ እያለ ፡ ገንዘባችንን ፡ ሊያስበላብን ፡ ወዲያው ፡ ተርቤ ፡ አላበላችሁኝም ። ተጠምቼ ፡ አላጠጣችሁኝም ። ታርዤ ፡ አላለበሳችሁኝም ። ታምሜ ፡ አላየችሁኝም ። እንግዳ ፡ ሆኜ ፡ አልተቀበላችሁኝም ። ታሥሬ ፡ አልጠየቃችሁኝም ፡ ይላል ። ይህን ፡ ያህል ፡ ስድስት ፡ ቃል ፡ ምን፡ ያናግረዋል ። ወዲህ ፡ ለነገ፡ አታስቡ፡ ይላል፡ ወዲህ፡ አላበላችሁኝም ፡ ይላል ። ከኛ ፡ ወገን ፡ የተራበ ፡ የተጠማ ፡ የታረዘ ፡ የለም ፡ መስሎት ፡ ይሆን ፡ ተሰማይ ፡ ተሰዶ መጥቶ ፡ ተርቤአለሁ ፡ ተጠምቻለሁ ፡ ታርዣለሁ ። ምንድር ፡ ነው ፡ ሰማዩን ፡ ያህል ፡ ሰፈ ፡ አገር ፡ ይዞ ፡ አባቱ፡ ከዚያው ፡ አያበላውም ፡ አያጠጣውም ፡ አያለብሰውም ፡ ልጁስ ፡ ሲቀላውጥ ፡ ነውር፡ አይፈራምን ። እኛስ ፡ ለሰማይ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ አናበላም ፡ አናጠጣም ፡ አናለብስም ፡ ከዚሁ ፡ ከሉት ፡ ከድሆች ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጋራ ፡ ገንዘባችንን ፡ ተካፍለን ፡ እንበላለን፡ እንጠጣለን፡ እንለብሳለን ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዘወትር ፡ ንዝንዝ ፡ ምንድር፡ ነው፡ በወንጌል ፡ ገንዘባችንን ፡ ሊወርስ ፡ የጠም ፡ አዳር ፡ እያለ፡ ሊከፈለን ፡ አስፓል ፡ መሰል ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

እግዚአብሔር ፡ ፈሪ ፡ ነው ፤ እኛ ፡ ብንበድለው ፡ ልጁን ፡ ልክ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተዛምደህ ፥ ና ፡ ብሎ ፡ በልጁ ፡ ታረቀን ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ያድርጉኝ ፡ መስሎት ፡ ነው ፡ ለካ ፡ በየቤቱ ፡ ፍሬት ፡ አይታጣም ፡ እኛ ፡ ስለበደልነው ፡ የምንከሰውን ፡ እርሱ ፡ ከሰን ።

እንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ ሥጋችን ፡ ከሆነ ፡ በሰበብ ፡ ባስባብ ፡ ብለን ፡ እርስቱን ፡ እንካፈለዋለን ፡ ጥቂት ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መርፌ ፡ ትወጋ፡ እንደሚሉት ፡ እንኳን ፡ ልጁን ፡ ልክ ፡ ተዛመደን ።

የክርስቶስ ፡ ነገር ፡ አይጣ ፡ አስቸገረ ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተርቤ ፡ አላበላችሁኝም ፡ ይላል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አምስት ፡ እንጀራ ፡ ለአምስት ፡ ሺህ፡ ሰው፡ አብልቶ ፡ አትርፎ ፡ ያስነሳል ።

ለበሬ ፡ ቀንድ ፡ አለው ፡ ለንጉሥም ፡ ዘውድ፡ አለው ፤ እረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምንሰጠው ፡ ክብር ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ እንለይለትምን ፤ አምልኮ ፡ ስግደት ፡ ምሥጋና ፡ ለርሱ ፡ ነው ፡ በጣም ፡ እንገዛው ፡ እንለማመጠውም ። እንታጠቅለትም ። ታላቅ ፡ ጌታ ፡ ሰፊ ፡ ነሽ ፡ ነውና ።

አዳኝም ፡ ገዳይም ፡ እርሱ ፡ ነውና ። በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ። ሁሉም ፡ ከርሱ ፡ ነው ፡ የተገኘው ፡ ሁሉም ፡ የሆነው ፡ በርሱ ፡ ነው ። አለ ርሱ ፡ ምንም ፡ የሆነ ፡ የለም ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል፡ ለዘለ ዓለሙ ፤ አሜን ።

እግዚአብሔር ፡ ሩቅ ፡ ነው ፤ ጥበቡ ፡ አይታይምና እግዚአብሔር ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ቶሎ ፡ ይሰማልና ። እግዚ. አብሔር፡ መኰንን ፡ ነው ፡ ቶሎ ፡ ይፈርዳልና ። እግዚአብ

አይሁድ ፡ ከእንስሳ ፡ እንኳ ፡ ለይተው ፡ ነው ፡ የሚበሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ግን ፡ ወንድማቸውን ፡ ይበላሉ ።

ዮሐንስ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ ቢል ፡ አይሁድ ፡ ሳይበሉት ፡ ተሽቀዳደሙ ፡ አረዱት ። እነሆ ፡ አይሁድ ፡ ያረዱትን ፡ በግ ፡ አሕዛብ ፡ እየበሉ ፡ ወፈሩ ፡ ቁመታቸውም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ። እስራኤል ፡ ግን ፡ ከስሰው ፡ የማንም ፡ መጫወቻ ፡ ሆኑ ።

መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜስ ፡ አያውቅም ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፡ ይላል ። ክርስቶስ ፡ ባይሞት ፡ ለኔ ፡ መንግሥትን ፡ ማን ፡ ይሰጠኝ ፡ ኖሯል ። የርሱ ፡ ሞት ፡ እኔን ፡ ጠቀመኝ ፡ እሰይ ፡ እሰይ ፡ እንኳን ፡ የሞተልኝ ፡ እልል ፡ እልል ፡ እንግዲህማ ፡ ሥጋውንስ ፡ ብበላው ፡ ደሙንም ፡ ብጠጣው ፡ ምንነው ። እኔን ፡ የመሰላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ዳዊት ፡ ይሁዳን ፡ አገሩን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፡ እያለ ፡ ምን ፡ ይረግመዋል ፡ እርሱ ፡ ክልበላሁለት ፡ ብሎ ፡ ነውን ፡ እንዴ ፡ ይሁዳ ፡ ያለ ፡ መልክም ፡ ነጋዴ ፡ የለም ፡ የዘለዓለሙን ፡ ምግብ ፡ በ፴ ፡ ብር ፡ ሸጠልን ።

የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ አጅማ ፡ አድርጎ ፡ በረታ ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ሥጋ ፡ ነጥቆ ፡ ወስዶ ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ በቀራንዮ ፡ ሰቀለው ፡ ወይ ፡ አለማፈር ።

እግዚአብሔር ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ከሙሴ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ነቢያት ፡ ድረስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የማይሰማውም ፡ ታቦ ፡ ቃሉም ፡ ታሠረ ፡ እንግዲህ ፡ በምን ፡ ይነግራችሁ ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

አብ ፡ እሳት ፡ ወልድ ፡ እሳት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፡ ሰው ፡ ሶስት ፡ ቢሆን ፡ ከሩቤል ፡ ይጠነቁ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ምን ፡

ለእኅቷ ፡ ለማርታ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ትንሣኤ ፡ ሕይወት ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ። ወይም ፡ ተነሥቼ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለሁ ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ።

የዳዊት ፡ ቤት ፡ ግልገል ፡ አንበሳ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ተነሣ። ሰላሳ ፡ ብር ፡ ለይሁዳ ፡ ደስታው ፡ ነው ፡ ለክርስቶስ ፡ ግን ፡ ሢንቀቱ ፡ ሞቱ ፡ ነው ። ለክርስቲያን ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ገበያ ፡ ጥቅማችን ፡ ነው ።

ሙሴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጽፎ ፡ በሣጥን ፡ ከተተ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ይዋርን ፡ ብሉ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ወንጌልን ፡ ባይሰማ ፡ ነው ፡ በሣጥን ፡ አትሰብስቡ ፡ ማለቱ ። እነሆ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ከነሣጥኑ ፡ ወሰዱለት ። እኛስ ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በላነው ። የእኛ ፡ ሳጥን ፡ ልባችን ፡ ሆዳችን ፡ ነውና ፡ ጳውሎስም ፡ ሣጥኑ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ብሎናልና ።

አይሁድ ፡ ጅሎች ፡ ናቸው ። ክርስቶስ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደሁ ፡ ቢላቸው ፡ ከእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፡ ያውም ፡ እንጨት ፡ ከንእኞቱው ፡ መሰላል ፡ የሰማይ ፡ መውጫ ፡ ሆነ ።

እግዚአብሔር ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ሰደደ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተራበ ። እናንተ ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ በልታችሁ ፡ ምናልባት ፡ ባይበቃችሁ ፡ ደሙን ፡ ጠጡት ። ኦሪት ፡ ደም ፡ አትጠጡ ፡ እያለች ፡ ረሀብ ፡ ተሞታላችሁን ፡ ዛሬ ፡ ጠጥታችሁት ፡ ከሞት ፡ ዳኑና ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ ትገባላችሁ ። እናንተ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነጋዴዎች ፡ ከዚህ ፡ ከንቱ ፡ በግ ፡ ሥጋ ፡ ተቀራምታችሁ ፡ ዋጋው ፡ ስንቶቻችሁን ፡ ብትይዙ ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

እናንተ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያላችሁ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ ወሀችሁን ፡ ሊጠጣ ፡ መጥቷልና ፡ በጣም ፡ ደሙን ፡ ምጠጡት ፡ ጤና ፡ ይሆናችኋልና ፡ አትልቀቁት ።

ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ዓሣ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የተገኘ ። በብርብሬ ፡ የዓለም ፡ ኃጢአት ፡ የሰከረ ፡ ተይዞ ፡ በቀሬንዮ ፡ በሰቀል ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ አጠገበ ።

ሰይጣን ፡ በይሁዳ ፡ ልብ ፡ ገብቶ ፡ ክርስቶስን ፡ ቢያስገድል ፡ ምን ፡ ተጠቀመ ። ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተዘረፈ ፡ እንጂ ፡ ደባ ፡ ራሱን ፡ ስለት ፡ ድጉሱን ፡ እንደሚሉት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ እጅግ ፡ ተጎዳ ፡ እንጂ ፡ ማን ፡ ተጐዳለት ፤ ከገኛት ፡ የዘረፈው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ተመልሶ ፡ ገነት ፡ ገባ ።

ክርስቶስስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ እርባ ፡ ቀን ፡ ሠሉ ፡ ማንን ፡ ይሰልላል ። ሰማይንና ፡ ምድርንስ ፡ መውደዱ ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ደግሞስ ፡ እሁሩ ፡ ፍቱ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መውጣቱ ፡ ይህንስ ፡ ያህል ፡ ሥልጣን ፡ ለሰው ፡ መስጠቱ ፡ በእሥር ፡ ቀንስ ፡ ጳራቅሊጦስን ፡ ልኮ ፡ በሰናኦር ፡ የተለዋወጠውን ፡ ቋንቋ ፡ ለሐዋርያት ፡ ገልጦ ፡ ማናገሩ ፡ ምድርን ፡ መውደዱ ፡ አይደለምን ።

ይህንን ፡ ሁሉ ፡ እያደረገ ፡ መንግሥት ፡ ማስፋት ፡ ምንድር ፡ ነው ። ተመልሶ ፡ ባልታወቀ ፡ ቀን ፡ ለመምጣት ፡ አይደለምን ፡ እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፡ ምዕመናን ፡ የወንጌልን ፡ ሰላም ፡ ጥሩር ፡ አድርጋችሁ ፡ ሃይማኖትን ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይዛችሁ ፡ ተሰልፋችሁ ፡ ቆዩት ። ያለዚያ ፡ እሳቱን ፡ ለብሶ ፡ እሳቱን ፡ ጐርሶ ፡ ይመጣላችኋል ፡ በእሳቱ ፡ ላበትም ፡ ያጠፋችኋል ።

## ክፍል ፡ ፲፩ ።

ክርስቶስ ፡ አጻራሽ ፡ የተገኘ ፡ ለት ፡ ምን ፡ ብለን ፡ እን ፈክራለን ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ተነሡ ፡ የሃይማኖትን ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፡ የሰላምን ፡ ሰይፍ ፡ ታጠቁ ፡ ጽድቅን ፡ እናድናት ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ዱር ፡ ገብታለችና ፡ ቀንጆዬቱ፡ ቀንጠፉ ፡ ጠጅ ፡ ሥጋው ፡ ጌጡ ፤ ገመሮ ፡ ብሩ ፡ ኩራቱ ፡ ቀጋ ፡ ሆነው ፡ ሰውረዋታልና ፡ እየጣስናቸው ፡ እንሂድ ፡ ጽድቅን ፡ እናገኛታለንና ። እፁን ፡ ይዘን ፡ በጻራሹ ፡ ውስጥ ፡ ሳናፍር ፡ እንደንፈክር ።

ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትሏታላችሁ ፡ ነቢያትን ፡ ሁሉ ፡ የገደለች ፡ በመጨረሻውም ፡ ጌታዋን ፡ የሰቀለች ። አይደለችምን ፡ ትሠርቃለች ፡ ትቀጥፋለች ፡ ታመነዝራ ለች ፡ ከቶ ፡ ምንድር ፡ ናት ። ለካ ፡ አንተ ፡ አታውቃት ምን ፡ ባሪያ ፡ እኮ ፡ ናት ፡ አሉ ፡ እንደዚህ ፡ እመቤት ፡ መስላ ፡ የምትቀልጥብን ፡ ( የምትከራብን ። )

አሁን ፡ ምን ፡ ይሆነኝ ፡ ብላ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኩራት ፡ እመቤት ፡ እያለቻት ፡ አንድስ ፡ መልክ ፡ ቢስ ፡ አፈር ፡ መሳይ ፡ አሁን ፡ ባርነቷ ፡ አልታወቀብኝም ፡ ብላ ፡ ነውን ፡ እነሆ ፡ እመቤቷ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊትም ፡ ያደረገችውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሰምታለች ።

አሁን ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እያበራች ፡ የመጣች ፡ ለት ፡ ድምጢ ፡ ይጠፋል ። ውሀ ፡ ለመሆን ፡ ለመቅለጥ ፡ ብላ ፡ ነው ።

ከቶ ፡ ባሪያ ፡ ከባርነቱ ፡ አይወጣም ። እንድትጠፋ ፡ ባታውቀውን ፡ ይሆን ።

ያችስ ፡ እመቤቷ ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ አሰለቻት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ክፋት ፡ እየሰማች ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አፈጽም ፡ ብላ ፡ ነው ፡ መታገሰ ።

እንድርማማት ፡ ዖፊ ፡ ያሬድ ፡ የምትባል ፡ መልኳ ፡ ያማረ ፡ ነው ፡ ድምፁም ፡ የጣፈጠ ፡ ነው ። እንደዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በፍቅር ፡ ያጌጠች ፡ ያማረች ፡ የተሸለመች ፡ ናት ። በርኅራኄም ፡ የተዋበች ፡ ናት ፡ ቀሷም ፡ ወንጌል ፡ ነውና ።

ጉንዳን ፡ በደረሰበት ፡ እንደሚቆነጥጥ ፡ መናፍቃንም ፡ በደረሱበት ፡ ጤና ፡ የላቸውም ።

ሰማይ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ አንኳበብን ፡ የሚኖር ፡ ክቶ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ቀን ፡ ፀሐዩን ፡ ሌሊት ፡ ጨረቃንና ፡ ከዋክብትን ፡ ተሸልሞ ፡ ዘወትር ፡ እኔን ፡ እኔን ፡ እዩኝ ፡ እዩኝ ፡ እያለ ፡ ያደክመናል ፡ ምነው ፡ የናቀን ፡ ድሆች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ነውን ፡ ረሳው ፡ መሰለኝ ፡ የወትሮው ፡ እንዳይመስለው ፡ በላዩ ፡ የተቀመጠው ፡ ወንድማችን ፡ ነውና ። እርሱም ፡ ተመልሶ ፡ አሁን ፡ ይመጣል ። እንደዚህ ፡ የኩራ ፡ እንደሰም ፡ ለመቅለጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፊቱን ፡ እንዴት ፡ ያየው ፡ ይሆን ፡ ኩራቱም ፡ ምድር ፡ አስለቀቀቃል ። ምን ፡ ይሆናል ፡ እንደሚያልፍ ፡ አያውቅምን ።

ምድርንስ ፡ ተግዢአቸው ፡ ቢላት ፡ ገደልና ፡ ዱር ፡ በሕርም ፡ እየሆነች ፡ ለምን ፡ ታውከናለች ።

ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ አስተምራት ፡ ብሎ ፡ ቢሰድላት ፡ ልጁን ፡ አስደብድባ ፡ አስገደለችውና ፡ ዋጠችው ፡ ጤናም ፡ አልሆናት ፡ በዋጠችው ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ አስታወከት ።

ዳታንንና ፡ አቤሮንን ፡ መሰሏት ፡ ሳታላምጥ ፡ ዋጠችውና ፡ ከስታወከት ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡ ከሰማይ ፡ በባቱ ቀኝ ፡ ተቀምጧል ። ወንድማችን ፡ መሆኑን ፡ አታውቅምን ፡ የታዘዘችውን ፡ ትታ ፡ ለሆዷ ፡ እውጥ ፡ እውጥ ፡ ማለት ፡ ምንድር ፡ ነው ።

